# ሕዝባችንን እንዴት ከረሃብ መታደግ ይኖርብናል?

ከዳዊት ተመስገን

የኢትዮጵያ ህዝብ በአኩሪ ባህሉና የረጅም ጊዜ ታሪኩ ሲታወቅ የነበረውን ያህል ካለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ወዲህ ተፈጥሮ ባሳደረችበት ተጽዕኖ ሳይሆን በተለይ ወያኔና በውስጡ ያሉ ግብራብሮች በፈጠሩት የፖለቲካና የኢኮኖሚ ቀውስ ምክኒያት የኢትዮጵያ ህዝብ ለተደጋጋሚ ረሃብ በመጋለጡ አሳፋሪ ለሆነ የተመጽዎችነት ታሪክ ተዳርጓል። አሁንም እየተዳረገ ይገኛል። ይህን አሳፋሪና ቅስም ሰባሪ የረሃብ አደጋ ለማስቀረት ሐቀኛ ዜጎችና ተቆርቋሪዎች ቢታገሉና ቢጥሩም በአጋጣሚ ከጨበጧት ስልጣን ባሻገር ሌላ የማይታያቸው ወያኔ ለአለም ህዝብ 11% አደግን እያለ በውሸት ላይ የተመሰረተውን እድገት ብቻ ነው የሚለፍፈው ነገር ግን የኢትዮጵያ ህዝብ ውስጥ ውስጡን በችጋር እየተሰቃየ ያለውን ጉድ በውሸት ላይ የተመሰረተውን እድገት የዓለም ሚድያ ዕውን አድርጎታል።

ወያኔ በዓለም ፊት ዓይኑን በጨው አጥቦ ምፅዋት መቀበልን እንደክብር ህዝቡን በረሃብ መቅጣትን እንደ ትልቅ ዓላማ ተያይዞታል፡ ያንዣበበው የረሃብ አደጋ እንዳለፉት ወቅቶች ሁሉ በአየር ንብረት መዛባት (በድርቅ) ምክኒያት ብቻ ሳይሆን ይልቁንም በአመዛኙ በተዛባ የኢኮኖሚና የፖለቲካ አካሄድ እየተባባሰ በመሄዱ ነው። እንደሚታወቀው የወያኔ ውሸት ድንበር ያልከለለው ዘመን ያልገደበው እንደሆነ እናውቃለን። እውን አገራችን ህዝቧን ፍጡሯን መመገብና መስረታዊ ህይወት መለገስ የማትችል ድሃ በመሆኗ ነውን? አይደለም አገራችን ኢትዮጵያ በወንዞች በዓለም ስድስተኛ በአፍሪካ አንደኛ ናት። ሆኖም ግን በአሁን ሰዓት ህዝባችን በረሃብ አደጋ ላይ ይገኛል። ምክንያቱማ በዘረኛውና አምባገነን አገዛዝ የፖለቲካ የኢኮኖሚና የማህበራዊ አስተዳደር ብልሹነት የተቀነባበረ የሀገርና የህዝብ ሃብት ንብረት ምዝበራ ዝርፊያና ሙስና በህዝቧቿ ላይ እየተፈፀመ ያለው ግፍና በደል ወዘተርፈ እንደመስተዋት ቁልጭ ብሎ ይኸው እራሱ መስካሪው ረሃብ ሆነ።

የማዳበሪያን ዋጋን በከፍተኛ ደረጃ በመጨመርና ስርጭቱን በማሳነስ ልዩ ልዩ የምርት ማሳደጊያዎችን የውጭ ምንዛሪ ዋጋ ከፍ በማድረግ የገበሬውን የመግዛት አቅም በማዳከም በገበሬው መካከል የፖለቲካ/የስነ ልቦና አለመረጋጋት በመፍጠር ገበሬዎች ከቀያቸው በማፈናቀል ለውጭ ባለ ሃብቶች መሬታቸውን በመቸብቸብ በርካታ የምርት ተቋማት በማዘጋትና ስራተኞችን ከስራ በማፈናቀል በተለይም ወያኔ ለራሱ የፖለቲካ ማስፈፀሚያ ብቻ ትኩረት በመስጠቱ ከፍተኛ የምርት መቀነስ ተከስቷል። ከሁሉም በላይ የሚያሳዝነውና የሚያስገርመው ያንዣበበውን የረሃብ አደጋ አስቀድሞ ድብቅ ሆኖ እንዲቀር በመሞከሩ ነው ነገር ግን አልተሳካለትም የዓለም ሚድያዎች እውን አድርገውበታል። እንደውም በረሃቡ ሰለባ የሆኑትን ወገኖቻችንን ከአንዱ ክ/ሀገር ወደሌላ ክ/ሀገር እንዳይንቀሳቀሱ እያደረገ ይገኛል።

ህዝቡና የተቃዋሚ ሃይሎች ለችግሩ ትኩረት እንዳይሰጡ የሚያነሱትን ጥያቄ ወደ ጎን በመተው የአገሪቱን የገንዘብና የሰው ሃይል የአንድ የፖለቲካ ድረጅት ስልጣን ለማጠናከር ህዝባዊነት የጎደለው እንደ ቡሄ ዳቦ የጠፈጠፈው የአማራን ህዝብ የማይወክሉ ወያኔ በአደራጀው በስመ አማራ ድርጅት በሚባል ዓመታዊ በዓል ላይ በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ እንዲባክን እየተደረገ ይገኛል። ህዝቡ ለህይወት መሰንበቻ እፍኝ ጥሬና ወሃ በሚሻበት በአሁን ሰዓት ብዙ ሚሊዮን ገንዘብ ለተለያየ የግል ጥቅሞቻቸውና ለመሸታ በመባከኑ እጅግ ጨካኝና አረመኔያዊ ድርጊት ነው። ለመሆኑ በዚህ ጉዳይ ላይ የሃይማኖት አባቶች ነን የሚሉት ህዝባችን በረሃብና ስደት ሲሰቃይ ስለ እውነት የቆመ እንደ ቀደሙት አባቶች ስለ እውነት የሚመስክር የለም ማለት ነውን?

ከአገራችን የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከቀራጩ እስከ ንጉስ የሚያውቁትን በማስተማርና በመጠቆም ያበረከቱትን አኩሪ ተግባር ማየት ይቻላል።ይሁንና በዚህ ሰናይ ግብር ውስጥ በቅለው አደራ የተቀበሉ የሃይማኖት ምሁራን ስንቶቻችሁ ስለእውነት ቆማችኋል? ስንቶቻችሁ ስለእውነት እንመሰክራለን ብላችሁ ራሳችሁን መርምራችኋልን? በዘመነ ወያኔ ለሚያልፍ ዓለም የማያልፍ መጥፎ ስም ይዘዉ የሚነጉዱ፣ ለሥልጣን፣ ለሹመት የሚራኮቱ፣ ከቄስ እስከ ጳጳስ የአገርና የሕዝብ ይበልጡንም የፈጣሪውን አደራ ወደ ጐን በመተው ከእውነት ውጭ በስሜት የሚመሩ ጠቢቡ በመጽሐፉ ስለእነኚህ ሲያወሳ ሰውን መፍራት ወጥመድ ያመጣል በእግዚአብሔር የሚታመን ግን እርሱ ይጠበቃል ብዙ ሰዎች የሹምን ፊት ይሻሉ፣ የሰው ፍርድ ግን ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው፡፡ ይላል ያለፈው ትውልድ መልካም የሃይማኖትን ቅርስ እንደተወልን ሁሉ ሕብረትንና ወንድማማችነትን እንዳስተማረን እንደሰበኩ ሁሉ ያለፈውን ያን መልካሙን ትውልድ መሆን የለበትም እንዴ?

የዛሬው ትውልድ ከትላንቱ ትውልድ በተሻለ ዕውቀት ላይ ሳለ ሰለምን የተሳሳተ ይሆናል? የአዋቂ ልብ እውቀትን ይፈልጋል እውነትን ይሻል እንጂ ድንቁርናንና ሥልጣን ብቻ አይመኝም የጻድቅ ፍርድ ይጣመም ዘንድ ለሃጥእም ማድላት ተገቢ አይደለም፡፡ ስለ እውነት ቆማችሁ መታገል እንጂ ለመጣው ሁሉ አጐብዳጅ በመሆን ሕዝብን ማደናገሩ ወይም ማሳሳቱ ተገቢ ነውን? የሕዝብ አገልጋዮች እንደመሆናችሁ መጠን የሕዝብ ለቅሶ ለቅሶአቸው የሕዝብ ፍሰሐ ፍሰሐቸው መሆን ሲቻል ብቻ ነው። ስለዚህ በኢትዮጵያ ውሰጥ በቤተ ክርስቲያናችን ያሉ አባቶች ምን እየሰሩ ነው? የምንለው በየትኛውም ትውልድ የማይቆሽሸውን በየትኛውም መንግሥት የማይጨልመውን የእውነት ቃል ለሕዝባችን እናስተምራለን እንደምትሉት ሁሉ ሕዝባችንን ለበጐ ነገር በማነሳሳት የወያኔን ወይም አረመኔያዊ አገዛዝ በማስወገድ አገራችን ኢትዮጵያን ከርሃብና ከስደት መታደግ ይኖርባችኋል፡፡

ወደ ስብከት ለመሄድ እንዳልሆነ እንዲታወቅልኝ እሻለሁ። ጉዳዩ የሃይማኖት ተቋማትንም ስለሚመለከት ነው። ጹሑፌን ለመቋጨት ያህል ከማህበረሰባዊ አመለካከት አንፃር ግለሰብ የማህበረሰቡ ነጠላ አባል ነው። ልክ አንድ ብልታችን የመላው ሰውነታችን ነጠላ አካል እንደሆነው ወይም አንድ ብልታችን የመላው ሰውነታችን ነጠላ አካል እንደሆነው ሁሉ ማለት ብልታችን

ከአካላችን ተነጥሎ ምንም ውስጥ የማይገባ ከንቱ እንደሚሆነው እንዲሁ ግለሰብ ከማህበረሰብ ቢነጠል ተስፋ ቢስ ነው። ብሎኑ ወይም ባለጥርስ ብረቱ ማሽኑን ከማገልገል ውጭ እርባና እንደሌለው ሁሉ ግለሰብም ለማህበረሰብ ደህንነት የራሱን አስተዋጽኦ ማድረግ ተቀዳሚ ተግባሩ ነው። የሰው ልጅ የግለሰብነቱን ፍሰሐዎች ሊያገኝ የሚችለው ማህበረሰብ ጋር ተጣምሮ መብትና ግዴታውን አውቆ ሲንቀሳቀስ ነው የሚል ግምት አለኝ በማንኛውም መልክ የሚገኘውን ዕርዳታ አሰባስቦ ህይወት የማዳን ተልዕኮ ወደማንገቡ ማዘንበሉ እናም ህዝቡ በሞት አፋፍ ላይ እያለ ግን እርዳታ አቅርቦት ለማዳን ልዩ የዜግነት ደረጃን ወይም ወገንተኝነትን የሚጠይቅ ስለሆነ ይህ አስከፊ ረሃብ እስከሚወገድ ድረስ እርዳታዎችን በማሰባሰብ ለተራበው ህዝባችን የሚደርስበትን መንገድ መፈለግ መጅመር ጥረቱ ቢቀጥል በውጭ ያለን ኢትዮድያውያንም እጃን ሳያጥፍ ለተጎጂዎች እርዳታው ይደርሳል ባለው መንገድ ሁሉ በመለገስ ነገ አገር የሚገነቡና የሚያበለጽጉ ወገኖቹን በፍጥነት እንዲረዱ በውጭ ለሚገኘው ኢትዩድያ ወገኖቼ በዚሁ መልክቴን አደርሳለሁ። ረሃብተኞች የፖለቲካ ሰለባ ሊሆኑ አይገባም!!

የኢትዮድያ ሕዝብ የድል ባለቤት ይሆናል!

እናቸንፋለን!!

20 Nov 2015